# “አባት ፍንዳታ”

ከ ጎሳዬ ይመር

ቀደም ባሉት አመታት የአለማችን ሃብታም እና ድሀ ሀገራትን በየረድፍ በየረድፉ ለመለየት በዜና ማሰራጫዎች ሳይቀር ይቀርብ የነበረው አጠራር “ያደጉ” እና “ያላደጉ” ሀገራት በሚል ነበር። ይህ አይነት አጠራር በእንግሊዘኛ ሲነበብ “Developed” እና “Undeveloped” የሚለው ነው። አሁን-አሁን ይህ አይነት አጠራር ነውር (politically incorrect) ነው ተብሎ ስለሚታመን ከምድረ-ገፅ እየጠፋ ነው። የወቅቱ ትክክለኛ አጠራር “ያደጉ” እና “በማደግ ላይ ያሉ” ወይንም በእንግሊዘኛ (Developing) የሚለው ነው። “Undeveloped” የሚለው መጠሪያ እንዲቀር የተወሰነው ትርጉሙ ሲዘረዘር ከሌሎቹ ጋር እኩል ተወልዶ የማያድግ ወይንም የመከነ የሚል እንደምታ ያለው ነው ከሚል ነው። በዚህ የተነሳ ነው እንግዲህ “በማደግ ላይ ያሉ” የሚባል አባባል የመጣው።

እንደኔ . . . እንደኔ ግን የኢትዮጵያን የግሉን ፕሬስ ሁኔታ ስንመለከት ዘንድሮም “ያደጉ” እና “ያላደጉ” ወይንም “Developed” እና “Undeveloped” የሚባሉ የፕሬስ ውጤቶች አሉ! ገና በልጅነታቸው ህዝብን አጋጭተው . . . አመፅ አቀጣጥለው የከሰሙም ነበሩ (እነዚህ አይነቱ ገና ከየትኛው ረድፍ እንደሚፈረጁ ሳይታወቅ ነውና የጠፉት እዚህ ጋር እንዝለላቸው!)

ማንኛውም ሚዛናዊ አንባቢ ይስማማል ብዬ እንደምገምተው ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ወቅት እነ *“አዲስ-አድማስ”*፣ “Addis Fortune” እና “Capital” ጋዜጦች ያሳዩት የጥራት መሻሻልና የሙያ ብቃት “ያደጉ” የፕሬስ ውጤቶች የሚያስብላቸው ነው። ምክንያቱን በደንብ ለይቼ ባላውቀውም በተለይማ የእንግሊዘኛዎቹ ጋዜጦች እድገት ሁሉንም ያስገረመ ነው። ከእነሱ ጋር አብሮ-አደግ የነበረ እና እድገቱ አሁን “የመከነ” ወይንም እንደ ካሮት ተክል ወደታች የሚሄድ ደግሞ አለ - ሪፖርተር ጋዜጣ! ይህንን ጋዜጣ እንደው politically correct እንሁን በማለት “በማደግ ላይ ያለ” ብንለው ፌዝ ነው የሚመስልብን። የወቅቱ የሪፖርተር ጋዜጣ ትክክለኛ መገለጫው “ያላደገ” . . . ገፋ ካለ ደግሞ “የማያድግ” የሚለው ይመስለኛል! ይህ አጠራር እውነት ጋዜጣውን ይገልፀዋል ወይ የሚለውን ለመመለስ ትንሽ ዋቢ እንጥቀስ . . .

መቼስ አቶ አማረ አረጋዊ “ከቡር-ሚንስትር” በሚለው አምዱ ስር የሚፅፉቸውን ብልግናዎች እዚህ ጋር በዋቢነት ልጥቀስ ብል ይህንን ፅሁፍ እንዲያወጣልኝ የምጠይቀው ጋዜጣ ብልግና አናስተናግድም በማለት መጣጥፌን ወደ ቆሻሻ ቅርጫት እንዳይወረውሯት በመስጋት “ከቡር-ሚንስትር”ን ላልጠቀምበት እራሴ ላይ እቀባ ጥያለው። እስቲ ይታያችሁ . . . እድሜ ፈጅቶ 1000ኛውን የጋዜጣውን ህትመት ያቀረበን ጋዜጣ በድፍረት ዋቢ መጥቀስ ሲያስፈራ! በ1000ኛው የጋዜጣው ህትመት ላይም ሳይቀር “ከቡር-ሚንስትር” የሚል የብልግና አምድ ይዞ የሚወጣ ጋዜጣ “ያላደገ” ወይንም “የማያድግ” ነው እንጂ “በማደግ ላይ ያለ” ሊባል አይችልም። የሚያሳዝነው ጉዳይ ሪፖርተር ጋዜጣ ያኔ በብላቴናነቱ ወቅት ግሩም የሆነ አስተዋይ እና “የልጅ-ሽማግሌ” የተባለ ነበር . . . አሁንማ እድሜው ብስለት ሳይታከልበት ተቀልሎ-ተቀልሎ “አባት ፍንዳታ” ወይንም የተገላቢጦሹን “የሽማግሌ-ልጅ” የሚባል አይነት ወጥቶታል።

የሪፖርተሩ አማረ አረጋዊ ዘንድሮም እጅ-እጅ ያለውን የ “ከቡር-ሚንስትር” ብልግናውን በሃገሪቷ ባለሀብት ላይ እየጻፈ ይገኛል። እውነት ለመናገር ያኔ ሀይ. . . ሀይ የሚሉት ወገኖች ሳይቀር “ምን ነካው ይሄ ሰውዬ . . . . . ዘንድሮም እዛው ነው እንዴ?” ሲሉ ይደመጣሉ። “ያላደገው” ወይንም “የማያድግው” ሪፖርተር ግን ያኔ ጥለውት የሄዱበት ስፍራ ተቀምጦ የያኔውን አዝማች እየተቀኘ ነው! ጠ/ሚንስትር መለስ አንድ ወቅት “የሞኝ ዘፈን አንድ አይነት ነው” እንዳሉት አይነት! ከወራት በፊት አንድ በሀገር-ቤት የሚታተም ጋዜጣ ሲጽፍ አቶ አማረ አረጋዊ “የእርጥባን ምህዳሩ” ስለጠበበባቸው ያንኑ ቅኝታቸውን ሲቆዝሙ እንደሚሰነብቱ ዘግቧ ነበር።

ይሄ ደግሞ ግልፅ ሆኖ እየታየ ሪፖርተርን "በማደግ ላይ ያለ" ብሎ መግለፅ እንደው በጠቅላላው ስላቅ ነው የሚመስለው!

ሁላችንም እንደምናስታውሰው የሪፖርተሩ አማረ አረጋዊ "ሚድሮክ-ጎልድ" የተባለውን የሚድሮክ ኩባንያ አካል ድርጅት አንድ አመት ሙሉ "ግልፅነት የሌለው". . . "ለሃገር ብዙም ፋይዳ ያልሰጠ" . . . እና ሌሎችም በምድር ላይ አሉ የተባሉ ክሶች በሙሉ እየደረደረ ስሙን ለማስጠፋት እና ለማቆሸሽ ጥሮ ነበር። በአመቱ መጨረሻ የኢትዮጵያ ጥራት ሽላሚ ድርጅት (Ethiopian Quality Award Organization) እጅግ ብዙ መስፈርቶችን በማስቀመጥ በሀገሪቷ የሚገኙ የመንግስት እና የግል መስሪያ-ቤቶችን ሲያወዳድር ሶስት አሸናፊዎች ብቻ ነጥረው ወጥተው ነበር! እነዚህም ድንቅ መስሪያ-ቤቶች ለሃገር ለሰጡት አገልግሎት ሲባል በቤተ-መንግስት ከክቡር ፕሬዘዳንታችን የዋንጫ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በዚሁ የሽልማት ስነ-ስርአት ላይ በአምራች ድርጅቶች ዘርፍ በማእርግ ደረጃ የወርቅ ዋንጫና ልዩ የምስክር ወረቀት የተሸለመው የሪፖርተሩ አማረ አረጋዊ አመት ሙሉ የመንደር አሉባልታ ሲፅፍበት የከረመው "ሚድሮክ ጎልድ" ነበር። ይህ እንግዲህ የአማረ አረጋዊን የጋዜጠኛነት ውሎ ያሳያል! ሪፖርተር ጋዜጣ አመት-ከ-አመት ችክ በማለት በስም ማጥፋት ስራ ሲጠመድ ከሱ በኋላ የተወለዱት እነ "አዲስ ፎርቹን" ጋዜጣ በእድሜና በሙያዊ ክህሎት በመብሰል ጥለውት ሄደዋል . . . እነሱ በማስተዋላቸው "የልጅ-ሽማግሌ" ሲባሉ ሪፖርተር በተገላቢጦሹ "የሽማግሌ-ልጅ" ወይንም "አባት ፍንዳታ" ተብሎ ቀርቷል።

ሪፖርተር ጋዜጣ አንድ ሰሞን ደግሞ ሸራተን አዲስን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በእዳ ሊወርሰው ነው . . . ባንኩ በሚድሮክ ላይ ተቆጥቷል . . . አይነት ተረት-ተረት የዘገበ ሰሞን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቦርድ ለባለሀብቱ በፃፈው ግልፅ ደብዳቤ ላይ የሪፖርተር "ዘገባ" ተራ አሉባልታ መሆኑን እና ባንኩ ምንም እንደማያውቀው አትቷል። እንደውም እንደ ንግድ ባንክ ደብዳቤ ከሆነ ሚድሮክ እንደ ድርጅት ሆነ ባለቤቱ እንደ ባለሀብት እጅግ በጣም የሚያኮሩ ደንበኞች መሆናቸውንና ከነሱ ጋር ባንኩ ለመስራት በመቻሉ እድለኛነቱንም ገለጿል። በጣም የሚገርመው ጉዳይ ሪፖርተር እነዚህን "ዜናዎች" እየፈበረከ በሚፅፍበት ወቅት እራሱ አቶ አማረ ከአውሮፓ ትልቅ የህትመት መሳሪያ ላስገባ ነው በማለት ከወጋገን ባንክ ትክክለኛ አካሄድ ባልተከተለ መንገድ ትልቅ እዳ ወስዶ ነበር። በቅርቡ ኢትዮ-ቻናል ጋዜጣ ከወጋገን ባንክ በወጣ ማስረጃ እንዳሳየው አቶ አማረ አረጋዊ ቃሉን ሳይጠብቅ "የበሰበሰ" ማሽን ከዱባይ አምጥቶ ሲያበቃ ባንኩ በተያጅነት እንደያዘበት አንብበናል። ሚድሮክ ቤት ሲሆን ያልተፈጠረ ዜና የሚፈበርከው የሪፖርተር ጋዜጣ እራሱ አቶ አማረ አረጋዊ የፈረሰ ቤት ልክ እንዳለ አስመስሎ ከወጋገን ባንክ እዳ ሲወስድ ዝምታው ልክ እንደ ጨዋ ልጅ ነው! ይሄንን አይነት ጋዜጣ መቸስ "በማደግ ላይ ያለ" ማለት ሀጢያት ነው።

ባለፈው አመት ሪፖርተር ጋዜጣ አንዱ ስሙን ሊያጠፋው ሲቸከችክ የነበረው "ዳሽን ባንክ" በአመቱ መጨረሻ እንግሊዝ የሚገኘው የባንኮች ደረጃ መዳቢ መስሪያቤት የዚህ አመት የኢትዮጵያ ምርጥ ባንክ ብሎ እንደሸለመው ማቅረቡም የሪፖርተር ጋዜጣን "መምከን" ወይንም "አለማደግ" ያመላክታል። እንዲህ ... እንዲህ ... እያልን የሪፖርተርን "የሽማግሌ-ልጅነት" እናውራ ካልን አንድ አምድ ሳይሆን አንድ ጥራዝ ጋዜጣም የሚበቃ አይሆንም። ድሮ ሚድያን በተመለከተ በቲቪ ውይይት ሲደረግ ቀድሞ ይገኝ የነበረው አቶ አማረ አረጋዊ በቅርቡ ስለ ሀገራችን ሚድያ ይዘት በተመለከተ በኢቲቪ ቀርቦ እንዲወያይ በቃልና በፅሁፍ ሲጋበዝ እንቢ ብሎ ቀርቷል። ለነገሩ አልፈርድበትም . . . ያ ውይይት አቶ አማረ አረጋዊን እርቃኑን የሚያስቀረው ዝግጅት ነበር የሚሆነው! እንዴትስ ብሎ "ክቡር-ሚንስትር" የሚባል የብልግና አምድ አለኝ ብሎ መቅረብ ይችላል? ያ የኢቲቪ መወያያ መድረክ "የልጅ-ሽማግሌ" እና "የሽማግሌ-ልጅ" በግልፅ ተንገዋለው የሚለዩበት መድረክ ነበር። ሪፖርተር ጋዜጣ ከቲቪ ውይይቱ እራሱን በማግለል በፎርፌ "አባት ፍንዳታ" ተብሎ የተሰየመበት እና "በማደግ ላይ ያለ" ሳይሆን "የማያድግ" የሚል ተቀፅላውን ያረጋገጠበት ክስተት ነበር!! በሙያቸው የሚተማመኑት እነ "Addis Fortune" ጋዜጣ ግን መድረኩን በሚገባ በመጠቀም አቋማቸውን በበሳል ሁኔታ ሲገልፁ ተስተውለዋል። የሪፖርተርን ከኢቲቪው ውይይት መሸሽ በተመለከተ ማለት የሚቻለው . . . "አመል ያወጣል ከመሀል" ነው!

መስከንን "ለክቡር ጋዜጠኛ" ረጅም እድሜ ደግሞ "በማደግ ላይ" ላሉ ጋዜጦች እመኛለው!!